# አብዮታዊት ኢትዮጵያ

10




መስከረም ፲፮ ቀን ፲፱፻፷፱ ዓ.ም.

## ለውይይት መነሻ

አብዮታዊት ኢትዮጵያ ከቍጥር ፬ ጀምራ «ለነማርክስ ፍልስፍና አጭር መግቢያ» በሚል ርእስ ሥር በተከታታይ ትምህርታዊ የሆኑ የፍልስፍና ጽሑፎች ታቀርባለች ። እነዚህ ጽሑፎች የማርክሲዝምን ርእዮተ ዓለም ገና ለመጀመሪያ ጊዜ ለሚተዋወቁ የውይይት ክበቦች መነሻ ሃሳቦች እንደሚሰጡ ሆነው የቀረቡ ናቸው ።

# ፩· የጥንት የጋርዮሽ ዘመን

( ካለፈው የቀጠለ )

፮ኛ ትምህርት—ከን. ዓ.

### ፩. የጥንት የጋርዮሽ ዘመን

የኅብረተሰብ ታሪክ የሚጀምረው ሰው ለማምረቻ የሚሆኑ መሣሪያዎችን ሠርቶ በማምረት ከእንስሳት ከተለየበት ጊዜ አንስቶ ነው ። ይህ ዘመን የጥንቱ የጋርዮሽ ዘመን በመባል ሲታወቅ በመጀመሪያ ሰው ይኖርበት የነበረውን የኅብረተ ሰብ ኑሮ ዘዴ ያመለክታል ። ከአምስቱ ልዩ ልዩ ዘመናት በቀደምትነቱና በእርዝማኔው ብቻ ሳይሆን ማንኛውም ኅብረተሰብ ያለፈበት ሥርዓት በመሆኑ በአጠቃላይነቱ የታወቀው ይህ የጥንቱ የጋርዮሽ ሥርዓተ ማኅበር ነው ።

በዚህን ጊዜ የነበረው ስልተምርት ምን ዓይነት ነበር ? የምርት ኃይሎችን የተመለከትን እንደሆነ ለጊዜው የማይናቅ አስተዋጽኦ ቢኖራቸውም እጅግ ወደኋላ የቀሩ ነበሩ ። የሰው ዘር የሾለ ድንጋይ ፤ እንጨት ፤ የአጥንት ስባሪ ፤ . . . ወዘተ በእነዚህና እነዚህን በመሳሰሉ «መሣሪያዎች» በመጠቀም ሠርቶ ለማምረት ይጣጣር ነበር ። የምርት መሣሪያዎች እንዲህ ወደኋላ በመቅረታቸው በዚያን ጊዜ የሰው እውቀት ገና ያልዳበረ እንደነበረና እሱም የዚያኑ ያህል እጅግ ወደኋላ የቀረ እንደነበረ ያስረዳል ።

ከላይ እንዳልነው የምርት ኃይሎችና የምርት ግንኙነቶች የተያያዙ ናቸው ። እዚህ ላይ ታዲያ ግንኙነታቸው እንዴት ሊታይ ይችላል ? አደን ሲኬድ እንደዛሬው የተራቀቁ መሣሪያዎች ቢኖሩ አንድ ሰው ብቻውን ሄዶ አድኖ መመለስ ይችል ነበር ። በተጠረበ ድንጋይና እንጨት ግን መቾስ አንድ ትልቅ አውሬ ለመግደል ከተፈለገ ያንን መከበብ ደጋግሞ መምታትና በኅብረት መታገል ያስፈልግ ነበር ። በዚህ ላይ ደግሞ በዚያን ጊዜ «መሣሪያ» የሚባለው በረቀቀ ዘዴ ከፋብሪካ ውስጥ የሚሠራ ሳይሆን ሁሉም ያገኘውን ድንጋይ ወይም አጥንት ፤እንጨት ሾል ሻል አድርጐ የሚያነሳው ስለሆነ የምርት መሣሪያዎች ባለቤትነት ጉዳይ እስከዚህም አጨቃጫቂ አልነበረም ። መሬቱ ጫካው ፤ የኛ ይባል እንደሆን እንጂ የኔ ነው ተብሎ በግል የሚያዝበት ሁኔታ አልነበረም ።

ባጭሩ በዚያን ጊዜ የምርት ኃይሎች የጋራ ነበሩ ማለት ነው ። ስለዚህም የምርት ግንኙነቶች በእኩልነት ላይ የተመሠረቱ ነበሩ ። የምርት ኃይሎች የነበሩበት ደረጃ የምርት ግንኙነቶች በብዝበዛ ላይ እንደመሠረቱ ፈጽሞ አይፈቅድም ነበር። ምክንያቱስ ? ምክንያቱም በዚያን ጊዜ እንዲህ እጅግ ወደኋላ በቀሩ መሣሪያዎች የሚመረተው ምርት እጅግ አነስተኛ ነበር ። ለእያንዳንዱ የኅብረተሰብ አባል የሥራው ፍሬ ከእጅ ወደአፍ ትሆን እንደሆን እንጂ እምብዛም የምትተርፈው የለችም ነበር። እንደዚህም ስለሆነ ወንድ ፤ ሴት ፤ ወጣት ፤ ሽማግሌ ሲባል ሁሉም ቦታ ቦታውን ይዞ የአቅሙን ሠርቶ ማምረት ይገደድ ነበር እንጂ አንዱ ተቀምጦ ሌላው ሠርቶ ሊያበላው የሚችልበት ሁኔታ የለም ነበር ። ክፍያውም እንግዲህ የግድ ከእኩልነት ላይ የተመሠረተ ነበር ። ዝቅ ብለን እንደምናየው ብዝበዛ የሚባል ነገር የተጀመረው የምርት ኃይሎች ዳብረው አንድ ሰው በተሻሻሉ መሣሪያዎች እየሠራ ከራሱ አልፎ ሌሎችንም ለማኖር የሚችል ከፍተኛ ምርት ማምረት ከቻለበት ጊዜ

ጀምሮ ነው ። ማለትም የምርት ኃይሎች ዕድገትና መለወጥ የምርት ግንኙነቶችን ለውጠ በእኩልነት ሳይሆን በብዝበዛ ላይ የተመሠረቱ ግንኙነቶች ያደርጋቸዋል ። ይህንን ዝቅ ብለን እናየዋለን ።

ይህ የምርት ኃይሎች መሻሻል ኅብረተሰቡን ሙሉ በሙሉ ለውጦ ወደመደብ ኅብረተሰብ ከመለወጡ በፊት ግን ራሱ በብዙ የዕድገት ደረጃዎች አልፏል ። የቀድሞዎቹ መሣሪያዎች ቀስ በቀስ በጥንቃቄ እየተሠሩና እየተሻሻሉ ከመሔዳቸውም ሌላ ሰው ከሥራው እየተማረ ሌሎች አዳዲስ መሣሪያዎችን ማለትም ብረት ፤ መጥረቢያ ፤ ጦር ፤ ቀስት ፤ የዓሣ መያዣ መረቦች . . . . የመሳሰሉትን ከሁሉም ታላቅ ሚና የተጫወተውን እሳትን አገኘ ። በዚሁ አንፃር ደግሞ ቀስ በቀስ ወፍ ዘራሽ ፍሬዎችን ከመልቀም እሱው እየዘራ ማምረትን ማለትም እርሻን የዱር እንስሳትን ከማደን አልፎ ከብት ማርባትን ጀመረ ።

የምርት ኃይሎች ማደግና በተለይም ደግሞ የጦር ፤ የወንጭፍ ፤ መሠራት የሥራ ክፍፍል አስከተለ ። ወንዶች ሰውነታቸውም ተለቅ ያለና በተለይ ደግሞ የእርግዝናና የሕፃናት ማሳደግ ሸክም ስለሌለባቸው በይበልጥ ወጣ ወጣ እያሉ የማደኑን ተግባር ያዙ ። ሴቶች ፤ ሽማግሌዎችና ልጆች ግን ከአካባቢው ሳይርቁ ፍራፍሬ በመልቀምና በቤት ውስጥ በሚሠሩ ነገሮች ላይ አተኮሩ ። በተለይ ሽማግሌዎች ባላቸው የረዥም ጊዜ የሥራ ዕውቀት በመጠቀም ከቤት ቀርተው መሣሪያዎችን በማሻሻል በልዩ ልዩ ምክር ይረዱ ነበር ። በዚህም በመጠቀም የኅብረተሰቡን የአስተዳደር ጉዳይ ፈጻሚዎች ለመሆን በቁ ። (ቀስ በቀስ) በዚህ መሠረት በዕድሜና በጾታ የመጀመሪያው የሥራ ክፍፍል ተደረገ ።

ሥራንም እንደዚህ ተከፋፍለና ጥረትን አቀነባብሮ መሥራት በመጀመሩ ሰዎች ጥንት ያደርጉት እንደነበረው እንደመንጋ እየተንጋጉ መኖርን አቆሙ ። በቤተዘመድ መልክ የተደራጀ የመጀመሪያው ኅብረተሰብ ሥር ሰደደ ። ይህ የኅብረተሰብ ዓይነት የሚኖሩት ሰዎች በዕድሜና በጾታ በተደረገው የሥራ ክፍፍል በተቀነባበረ መልክ በመሠማራትና ተባብረው በመሥራት በኅብረት የሚኖሩበት ኅብረተሰብ ነበር ።

በዚህ ኅብረተሰብ ውስጥ የነበረው የምርት ግንኙነት በምርት ኃይሎች ዝቅተኛ ደረጃ የተወሰነ ነበር ። የኅብረተሰቡ አባላት በሙሉ በሥራ ይሳተፉ ነበር ። የሚያበረክቱትም ሥራ እንደየችሎታቸው ታይቶ የሚወድቅባቸው ኃላፊነት ነበር፤ ሰዎች በዚያን ጊዜ የነበራቸው የኑሮ ዓይነት መሬትን ፤ ጫካን ፤ የጋራ እንጂ የግል ሀብት ሊያደርግ የሚችል አልነበረም ። የምርት ኃይሎች በዝቅተኛ ደረጃ መገኘትና የጋራ ሀብት መሆንና ሠርቶ ለማምረት የሚያስፈልገው መተጋገዝ የምርቱ ክፍያም እኩልነት ላይ የተመሠረተ እንዲሆን አድርገውት ነበር ።

በዚህ ዘመን ለሴቶች የተሰጣቸው የሥራ ድርሻ ወንዶች ከተሰጣቸው የአደን ሥራ ይበልጥ የተረጋገጠና የማያቋርጥ የኑሮ ዋስትና የሚሰጥ ድርሻ ነበር ። ስለዚህም ሴት በኅብረተሰቡ ኤኮኖሚ ውስጥ ተቀዳሚውን ቦታ የያዘችና የቤተ ዘመዱዋ መሪ ነበረች ። በተለይ ደግሞ በዘመኑ ይደረግ የነበረው የጋብቻ ዓይነት የቡድን ጋብቻ እንጂ አንድ ወንድና አንድ ሴት ተነጥለው ባልና ሚስት አይባሉም ነበር ። ስለዚህ አንድ ሕፃን በተወለደ ጊዜ በርግጥ የሚያውቀው የናቱን ማንነት ብቻ እንጂ አባቱን የሚለይበት ዘዴ አልነበረም። ስለዚህ የቤተ ዘመዱ ሰብሳቢና የአመራሩን ቦታ የያዘችም ሴት ስለነበረች የዚህ ኅብረተሰብ አቋም ማትሪያርካ ወይም የሴት የበላይነት ላይ የተመሠረተ ነበር ።

ዝቅ ብለን እንደምንመለከተው የምርት ኃይሎች ተሻሽለው የወንዶች የምርት ሥራ ቀስ በቀስ በኤኮኖሚው ውስጥ ዋናውን ቦታ ሲይዝና ለኅብረተሰቡ በእርሻም ሆነ በከብት ርቢ በሚያስገኙት ምርት የተረጋገጠና የማያቋርጥ የኑሮ ዋስትና የሚሰጡት እነሱ ሆኑ ። ከግል ሀብት ጋር ያለው ግንኙነት ቀስ በቀስ በኅብረተሰቡ ውስጥ የበላይነት ቦታ ለወንዱ እየተሰጠ ፤ ሴት በሁለተኛ ደረጃ መሰለፍ ጀመረች ።



ኅብረተሰቡ እያደገ ሲሔድ ሰው ሠርቶ የሚያገኘውን ምርት ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ከፍ ከማድረጉም በላይ ሰውን ከዘላንነት ወደተደላደለ ኑሮ እንዲሔድ አደረገው ። ለመጀመሪያም ጊዜ አራሾችና ከብት አርቢዎች በሚል ኅብረተሰቡ በሥራ ዓይነት ተከፈለ ። ከዚያም የነዚህ ምርት በማደጉና ከኅብረተሰቡ አንድ ሌላ ክፍል ቀጥታ እህል ማምረት ሳይሆን በሌላ መስክ መሠማራት የሚችልበት ሁኔታ በመፈጠሩ የባለእጆች ሥራ እየተለየና እየተስፋፋ ሔደ ። እነዚህ ደግሞ በበኩላቸው የምርት መሣሪያዎችን እያሻሻሉ መሥራት ፤ የጦር መሣሪያ ፤ ልብስ ፤ ሸክላ ፤ ጫማ ፤ ይህንና ይህንን የመሳሰሉትን ሁሉ በማምረት ከአራሾችና ከከብት አርቢዎች ጋር በሚያደርጉት ልውውጥ ኑሮዋቸውን እያሟሉ መሔድ ጀመሩ ።

እንግዲህ ከዚህ ሁሉ የተነሣና ፴—፵ ሺህ ዓመታት ቀስ በቀስ በተጠራቀመ ዕውቀት በመጠቀም ሰው ለመጀመሪያ ጊዜ ለመኖር ከሚያስፈልገው በላይ ማምረት ጀመረ ። ትርፍ ምርት የሚባለው ተገኘ ። የዚህ ትርፍ ምርት መገኘት ይህ ነው የማይባል ለውጥ አስከተለ ።

ትርፍ ምርት ሰፊ የሆነ መገበያየት ያስችላል ። የመገበያየት መቻል ደግሞ አንድ ሰው የማያመርተውን ነገር ከገበያው ማግኘት ይችላል ማለት ነው ። ስለሆነም አንድ ሰው ከልዩ ልዩ ሥራዎች ከመሠማራት ይልቅ በያዘው አንድ ሥራ ተራቆና ሠልጥኖ ምርቱን ከፍ አድርጎ ገበያ ማውጣት የሚችልበት ሁኔታ ተፈጠረ ። ሁሉም በሞያው መሠልጠን ያዘ ። ልዩ ልዩ ኅብረተሰቦች በልዩ ልዩ ሥራ ሠለጠኑ ። በእያንዳንዱ ኅብረተሰብ ውስጥም የተለያዩ ሥራ የሠለጠኑ ክፍሎች እየዳበሩ ሔዱ ።

ከዚህ ጋር ተያይዞ በቀጥታ ከማምረት ሥራ ላይ ሳይሳተፉ የኅብረተሰቡን ኑሮ በማደራጀት ይረዱ የነበሩት ሰዎች ኅብረተሰቡ የሚያገኘውን የጋራ የሆነ ትርፍ ምርት ለግል ጥቅማቸው ማዋል ጀመሩ ። ከዚህን ጊዜ ጀምሮ በልዩ ልዩ ጐሣዎች መሐከል የሚደረጉት ግጭቶች መልካቸውን ለወጡ ። በፊት ጦርነት የሚደረገው ለጐሣው የተሻለ መሬት ለማግኘት ሲባል ነበር ። ድል የተመቱት ጐሣዎች ይባረሩ ይገደሉ ፤ ወይም ደግሞ ከአሸናፊው ጐሣ ተዋሕደው ይኖሩ ነበር ። አሁን ግን ጦርነት ሌላው ጐሣ የሚያፈራውንና የሚያጠራቅመውን ትርፍ ምርት ለመሰብሰብም ሆነ ከዚህም አልፎ ተርፎ ምርኮኞችን እንደቀድሞው ማባረርና መግደል ትቶ ይዞ ማሠራት የሚያዋጣ ነገር ሆኖ ተገኘ ። ምርኮኞች ወደባርነት ይለወጡ ጀመር ። በዚህ መልክ እንግዲህ የምርት ኃይሎች ማደግ ፤ የትርፍ ምርት መብዛትና ሰው ሰውን ሊበዘብዝ የሚችልበት ሥርዓት ተፈጠረ ማለት ነው ።

በዚህ መልክ ቀስ በቀስ የጋርዮሽ ሥርዓት እየበሰበሰ የግል ሀብት እየዳበረ ፤ አዲስ ዓይነት ቤተሰብ እየተፈጠረ ፤ ኅብረተሰብ በተቃራኒ መደቦች እየተከፈለ የመጀመሪያው በብዝበዛ ላይ የተመሠረተው ሥርዓት የባርያ ሥርዓት መሠረት ቀስ በቀስ ተጣለ ።

የጥንቱ የጋርዮሽ ሥርዓት መፈራረስና በአዲሱ የባርያ ሥርዓት መተካት የተከተለው ጐዳና በየትም ቢሆን የኅብረተሰቦች ዕድገት የተከተለው ብቻ አይደለም ። በተጨማሪ ከአንድ ኅብረተሰብ ሥርዓት ወደሌላ ወደከፍተኛ ሥርዓት ለውጥና ሽግግር በሚደረግበት ወቅት የምርት ኃይሎች ማደግ ምን ያህል የጠቅላላው የኅብረተሰቡ አንቀሳቃሽ ሞተር እንደሆነና ምን ያህል በማንኛውም መስክ የሰዎችን ኑሮ እንደሚለውጠው ያስረዳናል ።